# የሁለት ትውልዶች ወግ

## ከቀይ ሽብር እስከ ሰሃራ

### ክፍል ሁለት

ከበልጅግ አሊ
ተከታታይ ታሪክ

-፩-

ከወጣቶቹ ጋር ውይይት ካደረግን ከጥቂት ቀናቶች በኋላ አንዱ ከመካከላቸው ወደ ቤቴ መጣ። የመጣው አንድ የማስተረጉምለት ደብዳቤ ይዞ ነው። ስለ ደብዳቤው ይዘት ከተወያየን በኋላ ቀስ ብለን ሁለታችንም በየልባችን በጉጉት ወደምንጠብቀው ውይይት ገባን። ጨዋታችንን ቀጠልን።

በእጁ የያዘውን ወረቀት ፊቱን ቋጠር ፊታ እያደረግ እያየ <<ጋሼ እንዴት ነበር የከርቸሌ እስር ቤት?>> ብሎ ጠየቀኝ።

አሁን ተመልሼ ወደ ኋላ ሳየው ከርቸሌን እንደ እስር ቤት ማየት ይከብደኛል አልኩት ።ምክንያቱም ከመከራውና ከችግሩ ባሻገር ብዙ ነገር ተምሬበታለሁ። እንደምታየው ክራር መምታት፣ሹራብ መሥራት እዛ ነው የተማርኩት። መፅሐፍ ማንበብም በሰፊው የጀመርኩት እዛው ነው። መከራው ግን መከራ ነው።ምን ጊዜም በእኔም ሆነ በወቅቱ አብረውኝ ታስረው ከነበሩ ጓዶቼ አዕምሮ የሚጠፋ አይደለም። ከደርግ ፅህፈት ቤት እስረኛ ለመውሰድ በየቀኑ አንድ መኪና ሁለት ጊዜ ትመጣለች። ጠዋት የሚገረፉትን፣ማታ ደግሞ ለመግደል የሚፈልጓቸው ለመውሰድ ትመጣለች።መኪናዋ መጥታ እስከምትሄድ ጭንቀት፣ ከሄደች በኋላ ደግሞ ሃዘን ግቢውን ያጥለቀልቀዋል። የገዛ ስምህ ያስጠላሃል። ስምህ ቢረሳና ሳትጠራ ብትቀር ትመኛለህ። ጓደኛህን ከአጠገብህ ወስደው ገርፈው ፣ ሽባ አድርገው ያመጡታል ። ቁጭ ብሎ ሲጫወት የዋለውን ወስደው ይገሉታል። ማታ የተጠራው ልጅ በዛች ደቂቃ የሚችለውን ያህል ተናዞ ፣ ያለ ንብረቱን አውልቆ ሰጥቶ ውልቅ ይላል ። ላይመለስ ይሄዳል።እኔ ካለሁበት የተወሰዱና የተገደሉ ወጣቶች ፊት ዛሬም ከዓይኔ አይጠፉም። እሁድ ደርሶ ቤተሰቦች ምግብ ይዘው ልጃቸውን ሊጠይቁ ሲመጡ እቃውን ስንሰጣቸው የሚጮኹትን እናቶች አስባቸው። ልጄን አያለሁ ብላ የመጣች እናት የልጇ ጨርቅ ሲጠጣት የሚሰማትን መራራ ሃዘን አስበው።

ከጥቂት የዝምታ ደቂቃዎች በኋላ የእናንተስ ጉዞ እንዴት ነበር? አልኩት ከዛም ትንሽ ሲሰላስል ቆየና ስለ ሰሃራው ጉዞው እንዲህ ሲል ቀጠለ።

<<ይህንን አሁን የምትለኝን ስሜት ሰሀራ በረሃ ላይ ተሰምቶኝ ነበር። አንደ አብሮን የነበረ ልጅ ጉዟችንን በጀመርን በአስረኛው ቀን ደከመብን። መተንፈስ አቃተው። የመኪናውን ጣራ አንኳኩተን ሾፌሩ እንዲቆምልን ለመነው ። እየተነጫነጨ አቆመልን። ልጁን አወረድነው። ትንሽ እንደቆየ አረፈ።ቀበርነው።አሸዋ አለበስነው። ሁላችንም ደነገጥን ግን የማይለመድ የለምና ሞትንም ለመድነው። የደከመ ሰው ካልሞተ በስተቀር መኪናውን ማስቆም ተውን።መኪናው ቢቆምስ ምን ይጠቅማል። ጥላ የለ ፣መጠለያ የለ፣ ከሥር አሸዋ፣ ከጎን አሸዋ ፣ ከላይ ፀሐይና ንዳድ ። >>

<<ከሱዳን ወደ ሊቢያ መጓዝ በጣም ከባድ ነው። ከሁሉም የሚያስፈራው ከኸምሲን ነው። ከኸምሲን የበረሃ ውስጥ ነፋስ ነው።ከኸምሲን ሜዳውን ተራራ የሚደርግ ፣ አሸዋውን ከአንድ ቦታ አንስቶ ወደ ሌላ የሚከምር፣ ወቅቱን ያላወቀን ተጓዥ በቁሙ የሚቀብር፣ የሰው ልጆች ጠላት ነው። ከኸምሲን የሚነሳበትን ወቅት በልምድ የሚያውቁ የሰሐራ በረሃ ነዋሪዎች ጉዞ አይጀምሩም። በዚህ ምክንያት አምስት ወር ሱዳን ውስጥ ተቀመጥን። ከዛም የከኸምሲኑ ወቅት አልፏል ተብለን በሦስት ቶዮታ ላንድ ክሩዘር ተሞልተን ጉዟችንን ወደ ሰሜን አፍሪካ ሊቢያ አመራን። አሁን ጊዜው አልፎ ሲያወሩት እንዴት ይቀላል። መኪናው ሙሉ በሙሉ ዕቃ ተጭኖበት ከላዩ ደግሞ ሠላሳ ሦስት ሆነን ተጭነን

ለ6-7 ቀን የሚደርስ ምግብና ውሃ ይዘን ነበር።መኪናው ላይ አልተመቸኝም፣ ጠጋ በልልኝ፣ እግሬ ላይ ነው የተቀመጥከው፣ እግሬን ደነዘዘኝ በሚሉ ምክንያቶች መጣላት ጉዞውን እንደጀመርን የተለመደ ነበር።>>

<<ገና አንድ  ቀን እንደተጓዝን አንደኛው መኪና ሰለተበላሸ ሾፌሮቹ እሱን መጠገን ጀመሩ። ብልሽቱ ከባድ ሰለነበር አንዱ መኪና ተመልሶ ዕቃ ለማምጣት ይከንፍ ጀመር። እዛች ቦታ ተቀምጠን ሦስት ቀን አለፈ። የፀሐዩ ሙቀት ንዳድ ነው። ከስር አሸዋው ያቃጥላል።መነጋገር ቆመ ። መጠበቅ ፣መጠበቅ ፣ አሸዋ ፣አሸዋ ከሦስት ቀን በኋላ መኪናው ተሰራና ተነሳን።>>

<<ወደ ሰሃራ እየጠለቅን ስንመጣና የሚጠብቀን ጉዞ በጥል ሳይሆን በመስማማት እንኳ አዳጋች መሆኑን እያወቅን ስንመጣ ፣ በትንንሽ ምቾቶች መጣላታችንን አቆምን። ከሁሉ አስደንግጦ ዝም ያሰኘን  አንድ ቦታ አንድ የተበላሻ መኪና በአሸዋ ተሸፍኖ አገኘን። ሾፌሩ ጠጋ ብሎ ተመልክቶ በጣም በደነገጠ ሁኔታ ወደ እኛ ይመለከት ጀመር። >>

<<ሁላችንም እየሮጥን ወደዚያ ሄደን ስንመለከት የአንድ ሰው አፅም አየን።ምን አልባት ደክሞባቸው የተበላሸ መኪና ላይ ጥለውት ሄደው ይሆናል። እድላችን ከከፋ የሁላችንም መጨረሻ ይህ እንደሚሆን ገባን።ምግብም ሆነ ውሃ ከዛ ሰዓት ጀምሮ መቆጠብ ጀመርን። ሞት ለኛ እንደቀረበ ታሰበን። >>

<<አንድ ቀን ከመካከላችን አንዱ ልጅ ከመኪናው ላይ ወደቀ ። ሁላችንም መጮኽ ጀመርን። ከፊት የነበሩት የመኪናውን ጣሪያ ይመቱ ጀመር። አንድ ሁለት ኪሎሜትር ከተጓዝን በኋላ ሾፌሩ አቆመ። ወደ ኋላ ተመልሶ ልጁን እንደገና ጫነው።ሁኔታው በማናቸንም ሊደርስ ስለሚችል ፍርሃት ያሳድራል። ከዚያም የማያልቀውን መንገድ ተያያዝነው። አንድ የአሸዋ ክምር  ተራራ ላይ ስንደርስ ሾፌሩ ወርደን በእግር እንድንጓዝ ነገረን። መኪናዋ ቀስ ብላ ወደ ተራራው ጫፍ ብቻዋን ወጣች። ከስር አሸዋው ያቃጥላል። ከላይ ፀሐዩ ሌላ ነው። አራት ሰዓት የሚሆን በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ተጓዝን። ጋሼ አሁን ድካሙን ልነግርህ አልችልም። አንዳንዶቻችን እዛው ሞተን ብንቀበር ደስታውን አንችለውም። እንደምንም መኪናው ጋ ተደረሰ። ጉዞ ተጀመረ። ተኛን።በተኛንበት የለበስነው አንሶላ አሸዋ ይሞላዋል። ሰለመኝታው ምንም ልነግርህ አልችልም። ለመሆኑ እንዴት ነበር ከርቸሌ የምትተኙት ? >>

ከርቸሌ የመኝታችን ሁኔታ የተሻለ ነው። ወደ ደርግ ፅህፈት ቤት ከመወሰዴ በፊት አምስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ለአንድ ቀን አድሬ ነበር። እዛ ውስጥ አንዲት አራት በአራት በሆነች ክፍል ውስጥ ከስልሳ በላይ እስረኞች ነበሩበት። አሁን ሳስታውሰው እስር ቤት ለመጀመሪያ ጊዜዬ ነበርና ምንም እንዳልተኛሁ ነው። ከዛም ደርግ ፅህፈት ቤት የተወሰድኩት አነስተኛ ጠባብ ክፍል ነው።ወቅቱ አሰሳ (እናንተ ጠረጋ የምትሉት ዓይነት ) ነበርና ያቺ  ጠባብ ክፍል በአንዴ ሞላች። ውስጥ የተገረፉትም ፣ያልተገረፉትም አንድ ላይ ስለነበርን በጣም ተፋፍገን ነበር። እዛ የነበረው ሁኔታ በጣም አሰቃቂ ነው። መተኛት የለም ሁሉም ቆሞ ነው የሚያድረው። ሙቀቱም ቢሆን ከሰሃራ አይተናነስም።የተነፈስነው ትንፋሽ ዝናብ ሆኖ ይወርድብን ነበር።ከዛም ባለፈው እንደ ነገርኳችሁ ከብዙ ሰቃይ በኋላ ወደ ከርቸሌ ተወሰድን። በመጀመሪያ ከርቸሌ ውስጥ ሃኪም ቤት የሚባል ቦታ ነበር የተወሰድኩት። ከዛ ከኛ የባሰ የተገረፉ ፣ መንቀሳቀስ የማይችሉ ፣ ጥፍራቸው የተነቀለ ፣ ጣታቸው የተቆረጠ ፣ ጀርባቸው የተቃጠለ በብዛት ሲመጡ እኛ ደግሞ ትንሽ የተሻለን ወደ ዓለም በቃኝ እና ቀጠሮ ተዘዋወርን። እኔ ቀጠሮ ነበር የደረሰኝ። የታሰርንበት ክፍል ትልቅ ነው። ውስጡ የተለያየ የመተኛ ሁኔታዎች አሉ። በግድግዳው በኩል ብዙ ዓመት የታሠሩ እስረኞች በድሪቶ ( የተሠሰበሰበ አሮጌ ጨርቅ) የተሰራ ፍራሻቸውን ቆልለው እንደ አልጋ ይከምሩታል።በእስር ቤት አጠራር ሰኔቻ ይባላል።   ከክፍሉ አንድ በኩል ደግሞ የአለቀ የሸቦ አልጋ አለ። ይህ የሸቦ አልጋ እላይና እታችው አለው ። ክፍሉ መሃል ላይ የሚተኙት ደግሞ ደቦቃ ይባላል። ደቦቃ ላይ የሚተኛ ቀን ቀን ፍራሹን ማጠፍ አለበት። አለበለዚያ መተላለፊያ አይኖርም። የከርቸሌ መኝታ ፍራሽ ይገባ ስለነበር ከሁሉም የተሻለ ነው። ያም ሆኖ ይህ ከርቸሌም ቢሆን አስቸጋሪ ኑሮ ነበር።

ከዛስ እንዴት ሆናችሁ ሰሃራ በረሃ ውስጥ? ብዬ በተራዬ ጨዋታውን እንዲቀጥል ጋበዝኩት።

<<ሰሃራን አቋርጠን የሰው ዘር ለመጀመሪያ ያየነው ኩርፋ የሚባል የሊቢያ ከተማ ነው። እዛ ብዙ አልቆየንም። ሳር በጫነ መኪና ውስጥ ሆነን ወደ ቤንጋዚ ጉዞ አደረግን። የዛን ቀንም ሆነ ዛሬ ስለ እስር ቤት ስታወራን በደንብ እሰማህ ነበር። የዛን ቀን ከርቸሌ ውስጥ በጣም እንደተቸገራችሁ ስትነግረን በጣም በሃሳብ ስለተጠመድክ ዝም ብለን ሰማንህ። ከርቸሌ ለእኛ እንደ እረፍት ቦታ ነው የምንቆጥረው። >>

<< ከሊቢያ የተነሳሁት አንድ በሸራ በተሰራ ጀልባ ነው። ጀልባ ውስጥ ሃያ እንሆናለን። የጀልባው ሃላፊ ቱኒዛያዊ ነው። ስለ እሱ ብዙ ይወራል። ማንም ተጓዥ ጉዞውን ከመጀመሩ በፊት የሚጠይቀው ስለ ካፒቴኑ እውቀት ነው። አንዱ በህር ላይ ነው የተወለደው ባህሩን እንደ ጓዳው ነው የሚያውቀው ይላል፣ ሌላው ደግሞ የሊቢያ ባሕር ሃይል ነበር ይላል፣ ሌላው ባለፈው ሰንጥቆ በተጨበጨበለት ጊዜ ነው ማልታ ጠብ ያደረጋቸው ይላል። እንደ ንግዱ ብዛት የካፒቴኑ ገድል አብሮ ይነጉዳል። የካፒቴኑ ገድል ሲበዛ የመጫኛው ዋጋ ይንራል።ከብዙ ውጣ  ውረድ በኋላ እጣ ፋንታህ በሆነው ጀልባ መጫን ነው።ጉዞውን ስንጀምር በምሽት እየተዝናናን ነበር። በሕሩ ላይ ነጋብን። አንድ ትልቅ መርከብ በአጠገባችን ሲያልፍ መዕበል እንደሚነሳ በድምጽ ማጉያ ነግረውን ከባሕሩ እንድንወጣ አሳሰቡን።እኛ የምሄድበት ብቻ ስለምናስብ ሰለ ማዕበል የነገሩንን ማመን አልቻልንም። >>

<<ካፒቴኑ መመለስ አለብን አለ። እኛ አይሆንም አልን ። ከዛም ከጥቂት ሠዓታት በኋላ ማዕበሉ ጀመረ ። ያቺ ትንሽ ጀልባ ትናወጥ ጀመር።ማዕበሉ እየፀና እየበረታ ሲሄድ እንኳን መመለስን ልንቃወም የሕይወታችንን መትረፊያ መለመን ጀመርን ። ጀልባው ላይ የሚያስታውክ አለ፣ የሚያለቅስ አለ፣ የሚጮኽ አለ ፣ የሚፀልይ አለ። ጀልባዋ እላይ ደርሳ ትመለሳለች። ተመልሰን ወደ ሊቢያ ተጠጋን። የሊቢያ የባሕር ጠባቂዎች መጥተው አተረፉን። ሕይወታችን መትረፏን እንጂ ሊቢያ ውስጥ ምን እንደሚገጥመን አላወቅንም ነበር። የሊቢያ ፖሊሶች ያዙን። ታሰርን። እስር ቤቱ በጣም ይሞቃል። ሁሉም ነገር ያስጠላል። እኔ ለአንድ ዐረብ እሰረኛ ተላላኪነት ተመደብኩ። መጀመሪያ ምንም አልመሰለኝም ።  ለሥራ ብቻ የሚፈልገኝ ብቻ ነው የመሰለኝ። አንድ ሁለት ቀን ካደርኩ በኋላ ሰውነቴ መለስ አለ። ልብስም ተሰጠኝ። ገላዬን ታጠብኩ። ማታ ላይ ያ ዐረብ እኔ የምተኛበት መጣና አጠገቤ ለመተኛት ሞከረ። እንቢ አልኩት። በበነጋታው ደበደበኝ። ሌሎችም አገዙት። አሰቃየኝ። ሲኪኒ (ጩቤ) አወጣና ቂጤ ላይ ወጋኝ። በሶስተኛው ቀን ተመልሶ መጣ። አሁን ግን ከጓደኛው ጋር ነው የመጣው። እጄን ያዙኝ። ሱሬዬን አወለቁት። በሰው ላይ ይደረጋል የማልለው በእኔ ላይ ደረሰ።ሰውነቴን ሁሉ ሰቀጠጠው። ደሜ ፈሰሰ። ሰው ጠላሁ። አንተ ጨርቅ ነው አፍህ የጎሰጎሱት፣ እኔን ግን ተወኝ ጋሼ ይቅርብህ ባትሰማው ይሻልሃል። እኔ ከአሁን በኋላ ሰው አደለሁም። እረከሼአለሁ። በሕይወቴ አንድ ነገር እመኛለሁ። ያንን ዐረብ አግኝቼ በተበቀልኩት።አቅሙም ግን የለኝም። ቂሙ ሆዴ ውስጥ አለ። የተደላደለ የአውሮፓ ኑሮ እንኳ ይህ የደረሰብኝንን ያስረሳኛል ብዬ አላምንም>> አለኝ።

ይህንን ተናግሮ በጣም አለቀሰ ። እኔም አብሬው አለቀስኩ ። ይህንን የመሣሠሉትን ግፍ የሚፈፅሙትን  ዐረቦች ባገኝ እኔም የምበቀላቸው እንደሆንኩ ተሰማኝ። አዘንኩ። ከዛ ከበረሃ ተርፈው ያልፍልናል ሲሉ በሊቢያ እስር ቤት ለሚማቅቁ ኢትዮጵያውያን በሞላ አብረን አለቀስን።በረጅሙ ተነፈሰና ጨዋታውን እንዲህ ሲል ቀጠለ።

<<በአጠቃላይ ሲታይ የሊቢያ ሕዝብ ጥሩ አይደለም ። የተማረ ብዙ አይገኝበትም። ለኛ ለኢትዮጵያውያን ያላቸው ጥላቻ ብዙ ነው። ለእነርሱ ኢትዮጵያዊ ሆንክ ኤርትራዊ ምንም ልዩነት የለውም።በመንገድ ላይ መጥተው ያለህን ይቀሙሃል። ሲፈልጉ ይደበድቡሃል። ዘረኝነታቸውም ከማንኛው ይበልጣል። የእነርሱ መንግሥት እንዲማሩ ፣ እንዲያውቁ አይፈልግም። ጭካኔቸው ከማይምነት የመጣ ይመስላል። ይህ ደግሞ የብዙ ዐረቦች ፀባይ ነው። ለምሳሌ ሱዳን ውስጥ በእህቶቻችን ላይ የሚደርሰውን ላጫውትህ። ወደ ሊቢያ መሄድ የምትፈልግ ኢትዮጵያዊ ሴት በጣም ስቃይ ይበዛባታል። እያንዳንዱ በዚህ ቢዝነስ

የተሰማራ ማፊያ ያችን ልጅ መላጥ( የግብረ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ ) ይፈልጋል ። እንቢ ካለች አትሄጅም ብሎ ይከለክላታል። እሺ ካለች ደግሞ መከራ ነው ሱዳኖች በኮንደም ማድረግ አይወዱም። ብዙዎቹ ሴቶች የሰሃራን በረሃ የሚጓዙት እርጉዝ ሆነው ነው።አንዳንዶቹን ደግሞ እዛው ጉዞ ላይ ያስወርዳቸዋል። ሰሃራ ውስጥ የሚቀሩትን ቤት ይቁጠራቸው። ሴቶቻችን በመገደድ ብቻ ሳይሆን በገንዘብ እጥረት ሴተኛ አዳሪነት ይጀምራሉ። ይህ በተለይ ሊቢያ ውስጥ የጦፈ ቢዝነስ ነው። አንድ ሴት ሻይ ቤት ተቀጥራ ከሠራች የምትሠራው ይታወቃል። በድብቅ ትሸቅላለች ማለት ነው። እህቶቻችን እንደዚህ እየሠሩ ለእኛ ገንዘብ ሲጎልብን ይሞሉልናል። በጠገበ ዐረብ እየተደበደቡ በስቃይ የሚኖሩ ብዙ ናቸው። ለእኔ ዐረብ በእኛ ላይ የፈፀመው ግፍ ከጣሊያን ወረራም ከቀይ ሽብርም በላይ ነው። ምንአልባት  በሃገርህ ሰውና በሌላ ሃገር ሰው መጠቃት የተለያየ ሊሆን ይችላል።ለተጠቃው ሰው ግን የግፉን ጥልቀት አይቀንሰውም። ጋሼ በኛ ላይ የደረሰው ከቀይ ሽብር አይተናነስም። ይህ የምነግርህ ትንሹን ነው። እሲኪ ከሴቶቹ ተግባባና ያጫውቱህ ። የኛ ሴቶች አይን አፋርነት ሰላላቸው እውነቱን ግልፅ አድርገው አይነግሩህም ። ቢነግሩህ ግን ምን ያህል  ጠንካራ እንደሆንን ትገነዘባለህ ። የተሰቃየነውን ተሰቃይተን አውሮፓ ገብተናል። >>

<<ዐረቦቹ እስር ቤት ውስጥ ያለኝን ገንዘብ ሁሉ ወሰዱብኝ። ድሮ እስር ቤት ውስጥ <<የሻማ>> እንደሚባለው ማለት ነው። ይህንን እንኳ እኔ አላውቅም ነበር ሌሎች ሲወሩ ነው የሰማሁት። እድሜ ለኢሕአፓ የሻማን አስቆመ ብለው ሲወሩ አዱ ገነት እያለሁ ሰምቼ ነበር። ለምንድነው ኢሕአፓ <<የሻማ>> መክፈልን ያስቆመው? ብሎ ጠየቀኝ።

እኛ እስር ቤት በነበርንበት ወቅት የሻማ የሚባለው ድብደባ አልነበረም። ግን ሲወራ እንደሰማሁት አንድ አዲስ እስረኛ እንደመጣ  ያለውን ንብረቱን ለሻማ እንዲሰጥ ይጠይቁታል እንቢ ካለ ይደበድቡታል ። ያሰቃዩታል ። የኢሕአፓና የኢሕአወሊ አባላት መታሰር ከጀመሩ በኋላ ግን ይህ አስቃቂ ተግባር አስቆሙት ። ሁሉም በፍቅር ያለውን ተካፍሎ መብላት ተጀመረ። የወንጀል እስረኞች በፖለቲካ እስረኞች እየተመሩ እስር ቤቱን የፍቅር ቤት አደረጉት። እዛው እስር ቤት ውስጥ ወንጀለኛ የነበሩ በኢሕአፓ አቋም አምነው ወደ ፊት ጥሩ ተግባር ለመፈፀም የወስኑ ብዙ ነበሩ።

ጋሼ << ኢሕአወሊ >>  ምን ማለት ነው ?

ይቀጥላል።

beljig.ali@gmail.com